፫ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ይኸው ፡ ፈላስፋ ፡ ለመናፈስ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ፡
ወደ፡ ሰማይ ፡ አንጋጦ ፡ ስለ ፡ ከዋክብት ፡ ያስብ ፡ ነበርና ፡ በነገሩ ፡ ልቡ ፡ ስለ ፡
ተመሠጠ ፡ ከመንገድ ፡ ወጥቶ ፡ ተሰናክለና ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ቢወድቅ ፤ ከቤተ፡
ሰቡ ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ አንድ ፡ አሮጌት ፡ ሮጣ ፡ ሄዳ ፡ ከጕድጓድ ፡ እንዲወጣ፡
ረዳችው ። እሱም ፡ አቡዋራ ፡ ለብሶ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ጣሌስ ፡ ሆይ ፡ እግ
ሮችህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ራስህን ፡ በከዋክብት ፡ መኻከል ፡ እንዳታደርግ፡
እመክርሃለሁ ፡ አለችው ። ስለዚህ ፡ አያሎች ፡ ሰዎች ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠች ፡ ፈላ
ስፋ ፡ አሮጊቷ ፡ ሴት ፡ ናት ፡ ይላሉ ።

፬ ፤ ደግሞ ፡ ፒታኩስ ፡ የተባለው ፡ ፈላስፋ ፡ ዐቅሙን ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡
ነበር ፡ ተብሎ ፡ ይወራለታል ። እርሱ ፡ በሚኖርበት ፡ በአገሩ ፡ ምንም ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡
ዐይነት ፡ ወይን ፡ ቢኖር ፡ ከውሃ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይጠጣም ፡ ነበር ።

፭ ፤ ቢያስ ፡ የተባለው ፡ ፈላስፋ ፡ ፮፻፲፯ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ነበር ።
አንድ ፡ ቀን ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ በአንድ ፡ ትልቅ ፡ ዓሣ ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡
አገኙ ። በወርቁም ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ጠቢብ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጽፎበታል ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሕዝቡ ፡ አሳብ ፡ ቢያስ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ጠቢብ ፡ ስለ ፡ ታሰበ ፡
የተጻፈበትን ፡ ወርቅ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሰደዱት ።

፮ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢያስ ፡ ለወርቅና ፡ ለብልጽግና ፡ ጥንቃቄ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ነበር ።
አንድ ፡ ጊዜ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ በጠላት ፡ ተወረረና ፡ የአገሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገንዘባቸ
ውን ፡ ለመሠወር ፡ ሲያረብዱ ፡ ቢያስ ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ሰብስቦ ፡ ሀብታም ፡ መባል፡
ጨዋታ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ የኔ ፡ ዋናው ፡ መዝገቤ ፡ አእምሮዬ ፡ ነው ። እያለ ፡ ያለአ
ሳብ ፡ ተዝንቶ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ኤፒሚኒድስ ፡ አንድ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ፈላስፋ ፡ ነበር ። መቼም ፡ አንባቢዎቼ ፡ የም
ነግራቸውን ፡ ታሪክ ፡ እጅግም ፡ አያምኑትም ። ነገሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።
አንድ ፡ ቀን ፡ በልጅነቱ ፡ ጊዜ ፡ የጠፉችውን ፡ በግ ፡ እንዲፈልግ ፡ ኤፒሚኒድስን ፡
አባቱ ፡ ስለ ፡ አዘዘው ፤ በጊቱን ፡ ፈልጎ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ቀኑ ፡ ሙቀት ፡ ነበርና፡
በመንገዱ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ ዋሻ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ። በዋሻው ፡ ውስጥ ፡
ሳለ ፡ እንቅልፍ ፡ ስለ ፡ ገረዘዘው ፡ በዚያ ፡ ተጋደመና ፡ ከፈለገው ፡ አብልጦ ፡
እንቅልፍ ፡ ወሰደው ።

፰ ፤ እንቅልፍ ፡ ወስዶት ፡ ቅስቅስ ፡ ሳይል ፤ ሳይነቃ ፡ አምሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ተኛ ። ለመተኛት ፡ ዐይኑን ፡ በዘጋ ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ነቅቶ ፡ ዐይኑን ፡
በከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አርጅቶ ፡ ሸብቶ ፡ ነበር ። ከዋሻው ፡ ተነሥቶ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ
ነበረበት ፡ መንደር ፡ አቅንቶ ፡ ሄደ ።

፱ ፤ አባቱ ፡ ሞቶ ፤ ቀድሞ ፡ ሲሄድ ፡ ሕፃን ፡ የነበረው ፡ አርጅቶ ፡ አገኘው ። ቀድሞ፡
የማያውቃቸው ፡ ቤቶች ፡ ተሠርተው ፡ ከተማው ፡ በማያውቃቸው ፡ ሕዝብ ፡ ተመ

ልተው ፣ አገኛቸው ። ኤፒሚኒድስ ፣ ትሸን ፣ እንቅልፍ ፣ ሸለብ ፣ አድርጎ፣ሳለ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ መለዋወጥ ፣ መደረጉ ፣ ለአሰበው ፣ እጅግ ፣ የሚያስደንቅ ፣ ነው።

ጥያቄ ።

፩ ፤ የግሪክ ፣ ፈላስፎች ፣ የተባሉት ፣ እነማናቸው ፣ ?

፪ ፤ ጣሌስ ፣ ማነው ፣ ? ወዴት ፣ ተወለደ ፣ ? ሰባት ፣ ጠቢባን ፣ የተባሉት ፣ ሰዎች ፣ ምንድናቸው ፣ ?

ስለ ፣ ጣሌስ ፣ ምን ፣ ይታሰባል ፣ ?

፫ ፤ ስለርሱ ፣ ታሪክ ፣ ንገረን ፣ ?

፬ ፤ ፒታኩስ ፣ ማነው ፣ ?

፭ ፤ ቢያስ ፣ የነበረው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? የቬስን ፣ ታሪክ ፣ ተናገር ።

፮ ፤ ስለ ፣ ብልጽግና ፣ ቢያስ ፣ የሚለው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? የኤፒሚኒድ ስን ፣ ታሪክ ፣ ተናገር ።

ምዕራፍ ፣ ፳፩ ኤውሮጳ ።

የግሪክ ፣ ፈላስፎች ፣ ታሪክ ።

፩ ፤ ፈላስፋው ፣ ፒታጎራስ ፤ ሰው ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ ነፍሱ ፣ ወደ ፣ እንስሶች ፣ወይም፣ ወደ ፣ ወፎች ፣ አልፋ ፣ ትሄዳለች ፣ እያለ ፣ ያምን ፣ ነበር ። አንድ ፣ ጊዜ ፣ የኔ ፣ ነፍስ ፣ በአንድ ፣ አሞራ ፣ አካል ፣ ውስጥ ፣ ነበረች ፣ እያለ ፣ ነገሩን ፣ አጠንከረ ። ወዳጆቼ ፣ ሆይ ፤ ይህን ፣ እውነት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ለማመን ፣ ያስቸግራል ።

፪ ፤ ሔራክሊቱስ ፣ የኤፌሶኑን ፤ ጨለማ ፣ ፈላስፋ ፣ ይሉት ፣ ነበር ። የሚናገረው ፣ ሁሉ ፣ ሰው ፣ ሊያስተውለው ፣ የማይቻል ፣ ነገር ፣ ነው ። እርሱም ፣ ሰው ፣ ሊያስተ ውለው ፣ የማይቻል ፣ ጥበብ ፣ የለም ፣ ይል ፣ ነበር ።

፫ ፤ ይህ ፣ ጠቢብ ፣ ሰውዬ ፣ ይቺ ፣ ዓለም ፣ የመከራ ፣ ስፍራ ፣ ናት ፣ ብሎ ፣ ከሰው ፣ በተገናኘ ፣ ቍጥር ፣ ምንም ፣ ቢሆን ፣ ዕንባውን ፣ ሳያፈስ ፣ አያልፍም ፣ ነበር ። ስለዚህ ፣ ሰዎቹ ፣ አልቃሻ ፣ ፈላስፋ ፣ ይሉታል ። በመጨረሻው ፣ ኑሮውን ፣ በተራሮች ፣ መኻ ከል ፣ ባሉት ፣ ዋሻዎች ፣ ውስጥ ፣ አደረገና ፣ ቅጠላቅጠሉን ፣ ምግብ ፣ አደርጎ ፣ እን ደ ፣ ተመኘው ፣ የመከራ ፣ ኑሮ ፣ ኖረ ።

፬ ፤ ዲሞክራቱስ ፣ የተባለ ፣ ሌላ ፣ ልዩ ፣ ፈላስፋ ፣ ተነሣ ። እርሱን ፣ ደግሞ ፣ ሰዎች ፣ ሣቂታው ፣ ፈላስፋ ፣ ይሉት ፣ ነበር ። ይህ ፣ ደግሞ ፣ በማልቀስ ፣ ፈንታ ፣ የከተማው ፣ ሰዎች ፣ እብድ ፣ እስኪሉት ፣ ድረስ ፣ አዘውትሮ ፣ አጥብቆ ፣ ይሥቅ ፣ ነበር ። ሲናገር ፣ ሳለ ፣ እውነት ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ይመስለኛል ፣ ይል ፣ ነበር ።

፭ ፤ ፈላስፋው ፣ ኢናጎራስ ፣ ሰማይ ፣ ከድንጊያ ፣ ነው ፣ የተሠራው ፣ ፀሐይም ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ የጋለ ፣ ብረት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ያምን ፣ ነበር ። የርሱ ፣ አሳብ ፣ ደግሞ ፣ ልዩ ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የጥንት ፣ ዘመን ፣ ሰዎች ፣ የምድርን ፣ መልክ ፣ ወይም ፣ ሁኔታ ፣ ፈጽመው ፣ አላወቁም ።

፮ ፣ ፈላስፋው ፡ ኤምፔዶክሌስ ፡ ሄደና ፡ በኢትና ፡ ተራራ ፡ አጠገብ ፡ በሲሲሊ ፡ ተቀመጠ ። ፊቱ ፡ የሚያስፈራና ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበር ። ሎርል ፡ ከሚባል ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ሠርቶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ነበርና ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያውቀው ፡ ነበር ። ሕዝቡ ፡ በጣም ፡ እንደብልህ ፡ ያስቡት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ይኸ ፡ አልበቃውምና ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ሊያስቡት ፡ ፈለገ ።

፯ ፣ አንድ ፡ ቀን ፡ ኤምፔዶክሊስ ፡ ትልቅ ፡ በዓል ፡ አደረገና ፡ ወዲያው ፡ ጠፋ ፣ ሁለተኛ ፡ አልታየም ። ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ቢያርግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አሰቡ ። ወዲያው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በኤትና ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ መሬቱ ፡ ተከፈተና ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ቮልካኖ ፡ ሲተፋ ፡ ከተከፈተው ፡ ጕድጓድ ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ ጫማ ፡ ተወረወረ ። ቢመረመር ፡ የኤምፔዶክሊስ ፡ ጫማ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ ፣ ያ ፡ ሰነፍ ፡ ሽማግሌ ፡ የደረሰበትን ፡ መከራ ፡ ለማወቅ ፡ አላስቸገረም ። ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሄዷል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እዲያስቡት ፡ ቮልካኖ ፡ በሚወጣበት ፡ ጕድጓድ ፡ ተወርውሮ ፡ መግባቱ ፡ ታወቀ ፣ አንባቢዎች ፡ ይህን ፡ ለማመን ፡ ያስቸግራቸዋል ።

፰ ፣ ሳቅራጥስ ፡ (ሶክራት ፡) ከግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ እጅግ ፡ ብልህና ፡ የተሻለ ፡ ፈላስፋ ፡ ነበር ። በውነት ፡ ጠቢብና ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲሰኖች ፡ የነበሩ ፡ የግሪክ ፡ ሕዝብ ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖር ፡ ስለአልፈለጉ ፡ መርዝ ፡ እንዲጠጣ ፡ አስገደዱት ።

፱ ፣ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ፈላስፋ ፡ ዲዎጄኔስ ፡ ነው ። ኑሮው ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ስለሆነና ፡ ደግሞ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ሁኔታውን ፡ እንደሚናከስ ፡ ውሻ ፡ የማድረግ ፡ ዐመል ፡ ስላለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ውሻው ፡ ዲዎጄኔስ ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

፲ ፣ የሱ ፡ ትምህርት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ትንሽ ፡ ደስታ ፡ ካለው ፡ ደስ ፡ ይለውና ፡ ይመስለዋል ፡ ይል ፡ ነበር ። ይህ ፡ ፈላስፋ ፡ ያለጫማ ፡ ይሄዳል ፣ ልብሱ ፡ ጨርታ ፡ ጨርቅ ፡ ሆኖ ፡ ኵረጆና ፡ የውሃ ፡ መያዣ ፣ በትርም ፡ ይይዛል ።
በኋላ ፡ ቀፎ ፡ መሳይ ፣ አበጅቶ ፡ ያን ፡ ሲገትት ፡ ይውልና ፡ ማታ ፡ ከውስጡ ፡ ገብቶ ፡ ይተኛል ።

፲፩ ፣ አንድ ፡ ቀን ፡ ዲዎጄኔስን ፡ ለማየት ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ መጥቶ ፡ ከፀሓይ ፡ ወገን ፡ ቆመና ፡ ጥላውን ፡ ስለ ፡ ጣለበት ፡ ፈላስፋው ፡ ብርድ ፡ ተሰማው ፣ እስክንድር ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ «ዲዎጄኔስ ፡ ሆይ ፡ ኑሮህ ፡ በችግር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አያለሁ ፣ በቀፎ ፡ ውስጥ ፡ ታድራለህ ፡ ይልቅስ ፡ የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ እንዲሆንልህ ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ፡» ቢለው ፡ ዲዎጄኔስ ፡ ሲመልስለት ፡ «ይልቅስ ፡ ፀሓዩን ፡ አትጋርደኝ ፡» አለው ፡ እንጂ ፡ ከንጉሡ ፡ አንዳች ፡ ማግኘትን ፡ ናቀ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፣ ፒታጎራስ ፡ በምን ፡ ያምን ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፣ ሄራክሊቱስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፬ ፣ ዴሞክሪቱስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?
ከሄራክሊቱስ ፣ ልዩነቱ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? አናግሳጎራስ ፣ እምነት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ኤምፔዶክሊስ ፣ ወዴት ፣ ኖረ ፣ ? ምን ፣ ያስብ ፣ ነበር ፣ ?
፭ ፣ ሕዝቡ ፣ አምላክ ፣ ነው ፣ እንዲሉት ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ?
፮ ፣ ሶክራት ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ? እንዴምን ፣ ሞተ ፣ ?
፯ ፣ ዲዎጂኔስ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? የርሱ ፣ ትምህርት ፣ እንዴት ፣ ነበር ፣ ? እንደምን ፣ ኖረ ፣ ?
ስለ ፣ ዲዎጂኔስ ፣ አጭር ፣ ታሪክ ፣ ንገረን ። ?

## ምዕራፍ ፣ ፳፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፣ ፈላስፎችና ፣ ባለቅኔዎች ።

፩ ፣ ስፍራ ፣ የለኝም ፣ እንጂ ፣ ስለ ፣ ግሪኮች ፣ ፈላስፎች ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ በነገርኋችሁ ፣ ነበር ። በ፬፻፳፱ ፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ የተወለደውን ፣ (ጵላቶ ፣ ) አፍላጦን ፣ የተባለውን ፣ ፈላስፋ ፣ ለማሳሰብ ፣ አልረሳሁም ። ፰ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ (የሶክራት) የሳቅራጥስ ፣ ተማሪ ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። የአፍላጦን ፣ ደቀ ፣ መዝሙር ፣ የነበረው ፣ (አርጣጣሊስ ፣ ) አርስቶትል ፣ የታላቁ ፣ እስክንድር ፣ መምህር ፣ ነበር ። ፔሪፓቴቲክስ ፣ የሚሉትን ፣ የፈላስፎች ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ ሠርቶአል ። ፔሪፓቴቲክስ ፣ ማለት ፣ ተንጐራዳጆች ፣ ማለት ፣ ነው ። አርጣጣሊስ ፣ ደቀ ፣ መዝሙሮቹን ፣ ሲያስተምር ፣ እየተንጐራደደ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ተንጐራዳጆች ፣ ይባላሉ ።

፪ ፣ ይህ ፣ አፍላጦን ፣ የተባለ ፣ ሰው ፣ እንደ ፣ ሌሎቹ ፣ የግሪክ ፣ ፈላስፎች ፣ መምህር ፣ ስለ ፣ ነበረ ፣ ብዙ ፣ ጕበዛዝት ፣ ለመማር ፣ ወደርሱ ፣ ይመጡ ፣ ነበር ። ትምህርቱን ፣ የሚያስተምር ፣ በአቴን ፣ አጠገብ ፣ ዛፎች ፣ ችፍግ ፣ ብለው ፣ ደብር ፣ በሚመስሉበት ፣ አካዴሚያ ፣ በምትባል ፣ ስፍራ ፣ ነው ፤ ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ አካዴሚ ፣ የተባለው ፣ ቃል ፣ ከዚያ ፣ ወዲህ ፣ የትምህርት ፣ ስፍራ ፣ ለማለት ፣ ይታሰባል ።

፫ ፣ መልካም ፣ ስም ፣ ስላ ፣ ነበረው ፣ ከልዩ ፣ ልዩ ፣ የዓለም ፣ ክፍል ፣ ብዙ ፣ ተማሪዎች ፣ ወደርሱ ፣ ተሰባሰቡ ፤ ስለ ፣ ሃይማኖት ፣ ትልቅ ፣ አሳብ ፣ ነበረው ። በጎነትንና ፣ እውነትን ፣ አስፋፍቶና ፣ አጣፍጦ ፣ ሲያስተምር ፣ የሚሰሙት ፣ ሁሉ ፣ እጅግ ፣ ደስ ፣ ይላቸው ፣ ነበር ። ግሪኮች ፣ ስለርሱ ፣ ሲናገሩ ፣ አፍላንጦን ፣ እንደ ፣ አምላክ ፣ አካል ፣ ነው ፣ ይላሉ ።

፬ ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ ሌሎች ፣ የታወቁ ፣ ፈላስፎች ፣ ነበሩ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የነርሱ ፣ ይቈዩና ፣ ስለ ፣ ቅኔ ፣ ገጣሞች ፣ እነግራችኋለሁ ። በቀድሞ ፣ ዘመን ፣ ዋናው ፣ ባለቅኔ ፣ ሆመር ፣ ነው ። ከሁሉም ፣ እርሱ ፣ የታወቀ ፣ ነው ፣ ብዬ ፣ በፊት ፣ ተና

ግሪያለሁ ። ይህ ፡ ታላቅ ፡ ሰውዬ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በወዴትስ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ እርግጡ ፡ አልታወቀም ።

፭ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፱፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታውቋል ። ቅኔውን ፡ እየገጠመ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ እየዞረ ፡ ይዘምር ፡ ነበር ። ኢሊያድና ፡ ኦዴሲ ፡ የተባሉ ፡ ቅኔ ፡ የሚሰበስቡለት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩት ። ስለ ፡ ሲኩርጉስ ፡ የሰበሰቡት ፡ ጠፍቶባቸዋል ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ፒሲስትራቱስ ፡ እንደ ፡ አዘዛቸው ፡ አዘጋጁት ። የጀግኖችን ፡ ሞያና ፡ ጣዖታቸውን ፡ ያከብራሉ ፤ አብልጠውም ፡ ያፈቅሩት ፡ ነበር ።

፮ ፡ ሌሎቹም ፡ ቅኔ ፡ የሚገጥሙ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ አያሎች ፡ ነበሩ ፤ ከነዚህም ፡ እኩሌቶቹ ፡ ታላቅ ፡ ስም ፡ አግኝተዋል ። ከነዚህም ፡ አናክሬዎን ፡ የተባለው ፡ ስለ ፡ ፍቅርና ፡ ስለ ፡ ወይን ፡ ጽፎአል ። ፒንዳር ፡ ብዙ ፡ ቅኔ ፡ ሰብስቦአል ፡ ቴዎክሪቱስ ፡ ባገር ፡ ተቀምጦ ፡ ስለ ፡ ወንዶችና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ እረኞች ፡ ዘፍኖአል ። ብዙ ፡ ዘፈኖችና ፡ ግጥም ፡ ገጣሞች ፡ ነበሩ ። ኤስኪሉስ ፤ ሶፎክሊስ ፤ ኡርፒድስ ፤ እነዚህ ፡ ብዙ ፡ ስለሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ የጻፉ ፡ ናቸው ።

፯ ፡ እንደምታውቁት ፡ የግሪክ ፡ ሕዝብ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ደናቁርት ፡ ናቸውና ፡ የስንፍና ፡ አሳብ ፡ ይጫወታሉ ። ምድር ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ክብ ፡ መሆንዋን ፤ በየዕለቱ ፡ ዙሪያውን ፡ እንደምትዞር ፡ ፀሓይ ፤ ጨረቃ ፤ ከዋክብት ፤ ታላላቅ ፡ ዓለማት ፡ ሆነው ፡ በሰማይ ፡ እንደሚዞሩ ፡ አያውቁም ።

፰ ፡ ስለዚህ ፡ በቅኔያቸው ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ጆግራፊና ፡ ስለ ፡ አስትሮኖሚ ፡ (የከዋክብት ፡ ዕውቀት ፡) ምንም ፡ የሚጠቅም ፡ ወሬ ፡ አልተገኘም ። በመልካም ፡ አገር ፡ ስለሚኖሩ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ሁለጊዜ ፡ በቅኔያቸው ፡ የሚያነሡት ፡ የተራራውን ፡ የወንዙንና ፡ የፈሳሹን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፱ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ሳይቀር ፡ ርኩስ ፡ አሳብ ፡ የመላበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያነኑ ፡ በቅኔያቸው ፡ አግብተውት ፡ ይገኛል ። ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ አማልክት ፡ የሚሉዋቸው ፡ በተራራ ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በወንዝና ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ የሚፈነጩ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ሁኔታቸው ፡ በቅኔያቸው ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ያስደንቃል ።

፲ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የነዚህን ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግጥም ፡ እናስታውሳለን ፤ በቅኔያቸው ፡ የጠሩዋቸውን ፡ ስፍሮች ፡ መንገዶች ፡ ጐብኝተዋቸዋል ፤ ባማረ ፡ አገጣጠም ፡ ስለ ፡ ገጠሙዋቸው ፡ እጅግ ፡ ልብ ፡ የሚያናውጽ ፡ ንግግር ፡ አለባቸው ። ይኸንንም ፡ ቅኔ ፡ የገጠሙት ፡ ከሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ጽላቶ ፡ የተወለደው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? የማን ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ። ኖሮአል ፡ ? አሪስቶትል ፡ ምን ፡ ነበር ፡ ?

፪ ፤ ጽላቶ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ኖሮአል ፡ ?

፫ ፣ የርሱ ፡ አሳብና ፡ ትምህርቱ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፬ ፣ ሆመር ፡ ምን ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ?

፭ ፣ ሆመር ፡ የነበረበት ፡ ዘመን ፡ መቼ ፡ ይመስላል ፡ ? እንደምን ፡ ኖረ ፡ ?

፮ ፣ አናክሬዎን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ፒንዳር ፣ ቲዎክሪቱስ ፣ ሌሎችም ፡ ባለቅኔዎች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፯ ፣ ግሪኮች ፡ የሚያውቁት ፡ ምንድው ፡ ?

፰ ፣ የጥንት ፡ ግሪኮች ፡ ግጥምና ፡ ቅኔ ፡ ስለ ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?

፱ ፣ ግሪኮች ፡ ባረመኔ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ምን ፡ ያደርጉበት ፡ ነበር ፡ ?
ይህ ፡ ቅኔ ፡ ለጥንታውያን ፡ ግሪኮች ፡ ምን ፡ ስሜት ፡ ይሰጣቸው ፡ ያስነሣባቸው ፡ ኖሮአል ፡ ?
የጥንት ፡ ግሪኮችን ፡ ቅኔ ፡ ዛሬ ፡ ያስታውስት ፡ ይሆን፤ ?

፲ ፣ ዛሬ ፡ መንገደኞች ፡ እያዩ ፡ የሚያደንቁዋቸው ፡ ስፍሮች ፡ በነዚህ ፡ ቅኔዎች ፡ ተነግረዋልን ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### የጥንት ፡ ግሪኮች ፡ ልማድና ፡ አኑዋኑዋር ።

፩ ፣ አሁን ፡ ባለቅኔዎችንና ፡ ፈላስፎችን ፡ እንተውና ፡ የጥንት ፡ ግሪኮችን ፡ አኑዋኑዋር ፡ እንመልከት ። ለወንዶቹ ፣ ተኒክ ፡ የሚሉት ፡ የውስጥ ፡ ቀሚስ ፡ አላቸው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ነጠላ ፡ ይደርባሉ ። ጫማቸውን ፡ በጠፍር ፣ ወይም ፡ በገመድ ፡ እግራቸው ፡ ላይ ፡ ይጠመጥሙታል ። ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ግሪኮች ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚደፉት ፡ ባርኔጣ ፡ የላቸውም ። በኋላ ፡ ግን ፡ በገጫቸው ፡ ላይ ፡ ወተብ ፡ አድርገው ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ባርኔጣ ፡ ሠሩ ።

፪ ፣ ሴቶች ፡ ግን ፡ መቾውንም ፡ እስከ ፡ ትከሻቸው ፡ የሚደርስ ፡ ዐይነ ፡ ርግብ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ያደርጋሉ ። በጠጉራቸው ፡ ላይ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ፊንጣ ፡ ያደርጋሉ ። በጆሮዋቸውም ፡ የኩክ ፡ ማውጫ ፡ ያንጠለጥላሉ ። የቀረው ፡ ልብሳቸው ፡ ነጭ ፡ ቀሚስ ፡ ሆኖ ፡ በሐር ፡ መታጠቂያ ፡ ይታጠቁታል ፣ መታጠቂያው ፡ እጥፍ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ጫማቸው ፡ ይወርዳል ።

፫ ፣ መቾውንም ፡ ግሪኮች ፡ ምግባቸው ፡ በቀን ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ማለዳ ፡ ፀሓይ ፡ ስትወጣ ፣ ሁለተኛ ፡ በእኩለ ፡ ቀን ፣ ሦስተኛ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፣ አራተኛ ፡ ማታ ፡ ዋናው ፡ ራት ፡ ነው ።

፬ ፣ የቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ግሪኮች ፡ ምግባቸው ፡ ማነኛውም ፡ ምድር ፡ የምታበቅለው ፡ ፍሬ ፡ መጠጣቸውም ፡ ውሃ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ የእንስሳ ፡ ሥጋ ፡ እንዲበላ ፡ ተለመደ ። ይህንንም ፡ እንደ ፡ ፈንጠዝያ ፡ አደረጉት ። ከግሪክ ፡ ከተሞች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የከባረ ፡ ወጥ ፡ ማሰናዳታቸው ፡ ታወቀላቸው ። ፊት ፡ እንዳመለከትኋችሁ ፡ እስፓርቶች ፡ የሚባሉ ፡ በውጪ ፡ ነው ። በዋና ፡ ምግባቸው ፡ ጥቍር ፡ ሾርባ ፡ አለበት ።

፭ ፤ ድኖቹ ፣ አንድ፡ ፣ ጊዜ ፣ አንበጣ ፣ ይበላሉ ። በመጨረሻ፡ቅጠላቅጠል ፣ ይበላሉ ። በጠቅላላው ፣ ግሪኮች ፣ ሥጋ፡ ይወዳሉ ፤ ሎቼውንም፡ ቢሆን ፣ መጠጣቸው፡ በረድ፣ ወይም ፣ ሙቅ ፣ ውሃ ፣ ነው ። በኋላ ፣ ግን ፣ ውሃውን ፣ በበረዶ ፣ እያቀዘቀዙ ፣ መጠጣት ፣ ለመዱ ። ወይን ፣ በጣም ፣ የተለመደ ፣ ነው ። እንዲያውም ፣ ሀብታሞቹ ፣ መልካም ፣ ሽታ ፣ መዓዛ ፣ ያለው ፣ ወይን ፣ በገበታቸው ፣ ላይ ፣ ያደርጋሉ ።

፮ ፤ ግሪኮች ፣ ጨዋታ፡ ወደ፡ አለበት ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ስፍራ ፣ የተጠሩ ፣ እንደ፡ ሆነ፣ አስቀድመው ፣ ሰውነታቸውን ፣ ደኅና ፣ አድርገው ፣ ከታጠቡ ፣ በኋላ ፣ ሽቱ ፡ በሰውነታቸው ፣ ሁሉ ፣ ይረጭበታል ። ወደ፡ ጨዋታው ፣ ቤት ፣ በደረሱ ፣ ጊዜ፡ እጅ፣ ለጅ ፣ ተያይዘው ፣ ያገቡዋቸዋል ። ያለዚያም ፣ ከንፈራቸውን ፤ እጃቸውን ፤ ጉልበታቸውን ፣ ወይም ፣ ጫማቸውን ፣ ይስማሉ ። አነሰም ፣ አደገም ፣ የነበረ፡ ልብስ፣ ይለብሳሉ ። የሚጠሩት ፣ እንግዶች ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ምንም ፣ ቢሆን ፣ በንድነት ፣ እንዳይጠሩ ፣ የተወሰነ ፣ ሕግ ፣ አላቸው ።

፯ ፤ በኋለኛው ፣ ትውልድ ፣ የምሥራቃውያንን ፣ ልማድ ፣ ተከተሉና ፣ በመከዳና ፣ በመጨጊያ ፣ መደገፍ ፣ ተለመደ ፤ እንጂ ፣ ሲበሉ ፣ ሳሉ ፣ ቁመው ፣ ወይም ፣ በግድግዳ ፣ ትንሽ ፣ ወደ፡ ኋላቸው ፣ ደገፍ ፣ ብለው ፣ ነበር ። ምግቡ ፣ ወዲያው ፣ በገበታ ፣ እንደ፡ ቀረበ ፣ እንግዶቹ ፣ ከመብላታቸው ፣ በፊት ፣ ከምግቡ ፣ ተቀንሶ ፣ ለጣዖታቱ ፣ ይቀርባል ።

፰ ፤ የጤና ፣ መጠጥ ፣ እንደምንለው ፣ እንደኛው ፣ ልማድ ፣ አላቸው ። ይህም ፣ በዚያ ፣ በሌሉት ፣ ወዳጆች ፣ ስም ፣ እንጂ ፣ በዚያ ፣ ለተገኙት ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። በየሰው ፣ ስም ፣ አድርገው ፣ ሊቤሽን ፣ የሚሉትን ፣ የወይን ፣ መሥዋዕት ፣ በምድር ፣ ላይ ፣ ፍልቅ ፣ አድርገው ፣ ያፈሳሉ ።

፱ ፤ ጨዋታው ፣ ሲያልቅ ፣ ለጣዖታቸው ፣ አንድ ፣ መዝሙር ፣ ይዘምራሉ ። ከዚህ ፤ በኋላ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኛቸውን ፣ ሙዚቃና ፤ ዘፈን ፤ ጭፈራም ፣ ያደርጋሉ ።

፲ ፤ የከበርቴዎቹ፡ ቤት ፣ በጥርብ ፣ ደንጊያ ፣ የተሠራ ፣ ነው ። ከነዚሁም፡ ብዙዎቹን፣ ያስጌጡዋቸዋል ። የሕዝቡ ፣ ቤት ፣ አብዝኃኙ ፣ በጭቃ ፣ የተገነባ ፣ ካብ ፣ ነው ።

፲፩ ፤ ግሪኮች ፣ በጦርት ፣ ጊዜ ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ መሣሪያ ፣ ይዋጋሉ ። ከወታደሮቻቸው ፣ እኩሌቶቹ ፣ ቀስትና ፣ ፍላፃ ፣ ሲይዙ ፣ እኩሌቶች ፣ ደግሞ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ ጦር ፣ ይይዛሉ ። ጦሩን ፣ ሰብቆ ፣ በታላቅ ፣ ኃይል ፣ ከወረወረው ፣ በላይ ፣ እንጣጠረበት ፣ ላይ ፣ ይወጋል ፣ እንጂ ፣ መሳት ፣ የለም ። እኩሌቶችም ፣ ደንጊያ፣ የሚወረውሩበት ፣ ወንጭፍ ፣ አላቸው ። መቸውንም ፣ ቢሆን ፣ ከጠላት ፣ ጋር ፣ ሲዋጉ ፣ ጋሻ ፣ ያነግባሉ ።

፲፪ ፤ በቀድሞ ፣ ዘመን ፣ ባሩድ ፣ ገና ፣ አልታወቀም ፣ ነበርና ፣ ጠመንጃና፣ መድፍ፣ የለም ፣ ነበር ። በዚያም ፣ ዘመን ፣ ውጊያቸው ፣ እግር ፣ በእግር ፣ ደረት፣ ለደረት፣ ተጋጥመው ፣ ነበር ። ፀብ ፣ ሲሆን ፣ አእምሮዋቸው ፣ ይለወጣል ። ጀግኖቹም ፣ ሲዋጉ ፣ በታላቅ ፣ ንዴትና ፣ ኃይል ፣ ነበር ።

፲፫ ፤ ሰው ፡ ሲባል ፣ እርስ ፣ በርሱ ፣ የመዋጋት ፣ ጠባይ ፣ ስለ፣አለው ፣ ከጠላት፣ ለመከላከል ፣ እንዲመቻቸው ፣ በየአገሩ ፣ ሁሉ ፣ የከተሞቻቸውን ፣ ዙሪያ ፣ በረ ጅም ፣ ግንብ ፣ ይከቡታል ። እንደዚሁም ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ሲደረግ ፣ ኖረ ፤ ሂዳ ችሁ ፣ ብትመለከቱት ፣ ዋና ፣ ዋናዎቹ ፣ ከተሞች ፣ ፈረንሳይና ፣ ጀርመን ፣ ሌሎ ችም ፣ አያሎች ፣ አገሮች ፣ በዚሁ ፣ አኳኋን ፣ ተጠብቀዋል ።

፲፬ ፤ በዛሬው ፣ ጊዜ ፣ የሆነ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ጠላት ፣ አንዲት ፣ ከተማ ፣ በከበበ ፣ ጊዜ፣ ግንቡን ፣ በመድፍ ፣ ያፈርሰዋል ። ወይም ፣ ባሩድ ፣ ከምድር ፣ ውስጥ ፣ ቀብሮ ፣ በእሳት ፣ ሲያስነሡት ፣ ይገለባብጠዋል ። በጥንት ፣ ግሪኮች ፣ ግን ፣ የሚደረገው፣ ባቴሪንግ ፣ ራምስ ፣ ይሉታል ። አንድ ፣ ከባዳ ፣ ደንጊያ ፣ ባንድ ፣ ግንድ ፣ ጫፍ፣ አድርገው ፣ ጀግኖቹ ፣ ባለ ፣ ኀይላቸው ፣ እየገፉ ፣ በብዙ ፣ ድካም ፣ አጋጭተው ፣ ግንቡን ፣ ያፈርሱታል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ በጥንት ፣ ግሪኮች ፣ ጊዜ ፣ ሰዎች ፣ ልብሳቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ጫማቸውና ፣ ባርኔጣቸው ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፪ ፤ የሴቶች ፣ የራስ ፣ መሸፈኛ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ጌጣቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? ሌላው ፣ ልብሳቸውሳ ፣ ?

፫ ፤ የጥንት ፣ ግሪኮች ፣ ልብሳቸውና ፣ ማዕዳቸው ፣ ምግባቸው ፣ ምንድነው ፣ ? ሥጋ ፣ ይበላሉን ፣ ? የእስፓርቶች ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፬ ፤ ስለ ፣ ድኆች ፣ ምን ፣ ያስባሉ ፣ ?
ግርኮች ፣ ሥጋ ፣ መብላት ፣ ይወዳሉን ፣ ? ምን ፣ ይጠጣሉ ፣ ?

፭ ፤ ጨዋታ ፣ ወግ ፣ አላቸውን ፣ ?
ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ በገበታ ፣ አቀማመጣቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
የእስያ ፣ ሕዝብ ፣ በገበታ ፣ ሲቀመጡ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ግሪኮች ፣ የእስያን ፣ ልማድ ፣ ይከተላሉን ፣ ?
መብላት ፣ ሳይጀመር ፣ ምን ፣ ይደረጋል ፣ ?
የጤና ፣ መጠጥ ፣ ብለው ፣ ምን ፣ ያደርጋሉ ፣ ?

፮ ፤ ሊቤሽን ፣ የሚሉት ፣ ምንድን ፣ ነው ፣ ?

፯ ፤ ምግብን ፣ ምን ፣ ይከተለዋል ፣ ?
የሀብታሞችና ፣ የድኆች ፣ ልማድ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲ ፤ የግሪኮች ፣ ቤት ፣ አሠራር ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?

፲፩ ፤ ግሪኮች ፣ የጦር ፣ መሣሪያቸው ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ባሩድ ፣ አላቸውን ፣ ?
ጀግኖች ፣ በጦርነት ፣ ጊዜ ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ እንዴት ፣ ይሆናሉ ፣ ?

፲፫ ፤ የከተማቸው ፣ ምሽግ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
በኤውሮጳ ፣ ምን ፣ ይታያል ፣ ?

፲፬ ፤ ባሁኑ ፣ ዘመን ፣ ምሽጉን ፣ እንደምን ፣ አድርገው ፣ ይይዙታል ፣ ? ጥንት፣ዘመን፣የከተማውን፣ቅጥር ፣ ሲንዱት፣እንዴት፣አድርገው፣ነው ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፹፬ ፣ ኤውሮጳ ።

### ፊሊጵ ፣ የመቄደንያው ፣ ግሪክን ፣ ድል እንደ ፣ አደረገ ።

፩ ፤ የግሪክን ፣ ታሪክ ፣ ከተውሁበት ፣ ስፍራ ፣እንደ ፣ ገና ፣ እነግዋለሁ። ስለ ፣ ቴቤ ያኖች ፣ ጦርነት ፣ ተናግሬ ፣ እንደ ፣ጨረስሁ ፣ አንባቢው ፣ ሳያስበው ፣ አይቀርም ። ሳይዘገይ ፣ ወዲያው ፣ ጦርነቱ ፣ እንዳለቀ ፣ የግሪክ ፣ መንግሥት ፣ ቅዱስ ፣ ጦር ነት ፣ ወደሚሉት ፣ ገባ ።

፪ ፤ የፎሲስ ፣ ሕዝብ ፣ በዴልፊ ፣ የአፖሎ ፣ መቅደስ ፣ ገንዘብ ፣ የነበረውን ፣ አርሰ ውት ፣ ስለ፣ተገኙ ፣ አምፊክቲዎኒክ በሚሉት ፣ ችሎት ፣ ከፍ ፣ ያለ ፤ መቀጮ፣እን ዲከፍሉ ፣ ተፈርዶባቸው ፣ ነበር ።

፫ ፤ ፎሲሶች ፣ መቀጮ፣ከመክፈል፣ለመዋጋት ፣ ስለ፣አሰቡ፣አቴኖች ፤ እስፓርቶች ፤ አካይያም ፣ የነሱ፣ረዳት ፣ ሆኑ ። ቴቤያኖች ፤ ሉክሬያኖች፣ቴሳሊያኖች፣ ወደ፣አም ፊክቲዎኒክ ፣ ጉባኤ ፣ ወገን ፣ ሆኑ ። ፊሊጵም ፣ የመቄዶንያ ፣ ንጉሥ ፣ ከነዚሁ ፣ ጋር ፣ ሆኖ ፣ መዋጋቱን ፣ ፈለገ ።

፬ ፤ አንዳንዶች ፣ ታሪክ ፣ ጸሓፊዎች ፣ የመቄዶንያን ፣ ግዛት ፣ ከግሪክ ፣ አውራ ጆች ፣ አንዱ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ይቈጥሩታል ። ሌሎቹ ፣ ግን ፣ ለብቻው ፣ የተለየ ፣ አገር ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ያስቡታል ። መንግሥቱ ፣ ከተመሠረተ ፣ አምስት ፣ መቶ ፣ ዓመ ት ፣ ሲሆነው ፣ ፊሊጵ ፣ በዙፋኑ ፣ እስኪቀመጥ ፣ ድረስ ፣ እንደ ፣ ኃይ ለኛ ፣ መንግሥት ፣ አይቈጠርም ፣ ነበር ።

፭ ፤ ፊሊጵ ፣ ዝና ፣ ወዳድና ፣ ጦርነት ፣ ፈላጊ ፣ ሰው ፣ ስለ ፣ ነበረ ፤ ገና ፣ ወታደ ሮቹ ፣ ወደ ፣ ግሪክ ፣ አገር ፣ ሲጓዙ ፣ ራሱን ፣ ለመላው ፤ ዓለም ፣ ንጉሥ ፣ አደ ረገ ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ግሪኮች ፣ እንደ ፣ ቀድሞዎቹ ፣ እንደ ፣ ሊዮኒዳስና ፣ እንደ፣ ሚልቲያድስ ፤ እንደ ፣ ኤፓሚኖዳስም ፣ ያሉት ፣ ጀግኖችና ፣ ድል ፣ አድራጎች ፣ መሪዎቻቸው ፣ አልነበሩም ።

፮ ፤ በዚያን ፣ ዘመን ፣ የታወቀ ፣ ተናጋሪ ፣ የነበረ ፣ ዴሞስቴኔስ ፣ የተባለ ፣ አንድ፣ አቴናዊ ፣ ፊሊጵን ፣ አስጨንቆት ፣ ነበር ። የአቴን ፣ ሰዎች ፣ ጦርነት ፣ አድርገው ፣ እንዲነሡበት ፣ ለማድረግ ፣ በፊሊጵ ፣ ላይ ፣ እጅግ ፣ የሚያስፈራ ፣ እነጋገር ፣ስለ፣ ተናገረበት ፣ ከዚያ ፣ ወዲህ ፣ ብርቱ ፣ እነጋገርን ፣ ፊሊጵክስ ፣ አሉት ።

፯ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ አቴኖች ፣ በ፫፻፴፰ ፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ በኪሮኒያ፣ ተዋግተው ፣ ድል ፣ ሆኑ ። ከዚያ ፣ ወዲያ ፣ ፊሊጵ ፣ የግሪክን ፣ አገሮች ፣ እስከ፣ ዕለተ ፣ ሞቱ ፣ ረግጦ ፣ ገዛቸው ። ምናልባት ፣ በውስጣቸው ፣ ከተገኙት፣ገዦች፣ ይልቅ ፣ እርሱ ፣ ለግሪኮች ፣ የተሻለ ፣ ገዢ ፣ ሳይሆን ፣ አይቀርም ።

፰ ፤ ዳሩ ፤ ግን፡እርሱም፡ብዙ፡ክፉት፡አያጣም ። አንዱ፡ዐመሉ፡ያለመጠን፡እየጠጣ፡ ክፉኛ ፡ ይሰክር ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ግብር ፡ አድርጎ ፡ ከገበታ ፡ እንደ፡ ተነሣ ፡ ችሎት ፡ አደረገና ፡ ባንዱ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ ፈረደበት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰውዬ፡ «ከሰከረው ፡ ፊሊጶ ፡ ወደ ፡ አልሰከረው ፡ ፊሊጶ ፡ ተማጥኛለሁ» እያለ ፡ ጮኸ ። ፊሊጶም ፡ ስካሩ ፡ ሲያልፍለት ፡ ሰውዬው ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳው ፡ ነገሩን ፡ አዛውሮ ፡ እንደ፡ገና ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ፈረደ ።

፱ ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ድኃ ፡ ሴት ፡ ጕዳዩዋን ፡ ለማመልከት ፡ ብላ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በከንቱ ፡ ከደከመች ፡ በኋላ ፡ ፊሊጶ ፡ ግን ፡ ነገ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ እያለ፡ከፊቱ፡ አስወገዳት ። በመጨረሻው ፡ አንችን ፡ የምሰማበት ፡ ጊዜ ፡ የለኝም ፡ ቢላት ፡ እርስዋም ፡ "ፍርድ ፡ ለማድረግ ፡ ጊዜ ፡ ካላገኘህ ፡ ንጉሥ ፡ መሆን፡አይገባህም" ስለ ፡ አለችው ፤ ፊሊጶም ፡ ሴቲቱ ፡ የተናገረችው ፡ ቃል ፡ እውነት ፡እንደ፡ሆነ፡ ተረዳውና ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለንጉሥ ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ተግቶ ፡ ይሠራና ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ።

## ግሪክ ።

፲ ፤ ግሪክን ፡ አሸንፎ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ የተቀመጠው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ብቻ፡ነው ። ከፊሊጶ ፡ ዘመዶች ፡ ባንዱ ፡ የተጠቃና ፡ የተበደለ ፡ ፖሳኒያስ፡የተባለ ፡ የዘበኞች፡ አለቃ ፡ የታወቀ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ከፒቴኑ ፖሳኒያስ ፡ አቤቱታውን ፡ እያቀረበ ፡ ቢያመለክት ፡ ፊሊጶ ፡ ቸለል፡እያለ፡አጥቂውን፡ባልቀጣ ፡ ጊዜ፡ፖሳኒያስ ፡ ራሱን፡ ለመግደል ፡ አሰበ ።

፲፩ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ የንጉሡ ፡ የፊሊጶ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሠርግ፡ነበርና፡ ንጉሡ፡ሕዝቡ ፡ ወደሚጫወቱበትና ፡ ሙሽሮች ፡ ወደ፡አሉበት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ፖሳኒያስ ፡ ሰይፉን፡ እንደ ፡ መዘዘ ፡ ገሠገሠና ፡ በደረቱ ፡ ሻጠበት ።

፲፪ ፤ የንጉሥ ፡ ፊሊጶ ፡ ሞት ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ መላው ፡ የአቴን ፡ ሕዝብ ፡ በእልልታና ፡ በደስታ ፡ አወካ ፤ ከሕዝቡም ፡ የሚበዙት ፡ ንጉሡን ፡ ስለ፡ገደለ ፡ ዋጋው፡ ነውና፡ለፖሳኒያስ ፡ የራስ ፡ ወርቅ ፡ ይገባዋል፡አሉ ። ሌሎችም ፡ የግሪክ ፡ አውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ በመቄዶንያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ዐመፁ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ቅዱስ ፡ ጦርነት፡የተባለው፡እንዴት ፡ ነው ፡ ? ጠንቁ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ?
ዴልፊ ፡ ከአቴን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ፎሲስ ፡ ቴሳሊ ፡ ምንድናቸው ፡ ?

፪ ፤ ወደ ፡ ፎሲያኖች ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ የተዋጋላቸው ፡ መንግሥት፡ ማነው ፡ ?
ወደ፡አሞፊክቲዮኒክ፡ወገን ፡ የሆነው ፡ ማነው ፡ ? ፊሊጶ፡ የመቄዶንያው፡ ንጉሥ፡የተዋጋው ፡ ወደየትኛው ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ መቄዶንያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? የተመሠረተው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
የፊሊጶስ ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ከመቄዶንያ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡
አለፉ ፡ ?

፮ ፤ ፊሊጶስ ፡ ማነው ፡ ? ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ ያደረገው ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?
በዚህ ፡ ዘመን ፡ ግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ፡ ?

፯ ፤ ዴሞስቴንስ ፡ ማነው ፡ ? በአቴኖች ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ?
ፊሊፒክ ፡ የተባለ ፡ ቃል ፡ ከጥንት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፰ ፤ የተመቱት ፡ ወዴት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?
ጦርነቱ ፡ የተጀመረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ሴሮንያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከቴቤስ ፤ ከአቴን ፤ ከስፓርታ ፤ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ፊሊጶስ ፡ ግሪክን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ገዛት ፡ ?

፱ ፤ ፊሊጶስ ፡ ማነው ፡ ? ስለርሱ ፡ ባጭሩ ፡ ትነግረናለህን ፡ ?

፲ ፤ ፖሳኒያስ ፡ ማነው ፡ ? የፊሊጶስን ፡ አሟሟት ፡ ተናገር ።
አቴኖችና ፡ ሌሎችም ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፹፭ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ታላቁ እስክንድር ድል መንግት ፤

፩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አዲሱ ፡ የመቄደንያ ፡ ንጉሥ ፡ እስክንድር ፡ ምንም ፡ የኻያ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፡ ባባቱ ፡ ዙፋን ፤ ለመቀመጥ ፡ የተገባው ፡ ነበር ። እርሱም ገና ፡ ሕፃን ፡ ሳለ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ዓለምን ፡ አሸናፊ ፡ ያሰኘውን ፡ የጀግንነቱን ፡ መግለጫ ፡ አስቀድሞ ፡ ስላሳየ ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ የተባለ ፡ ሁለተኛ ፡ ስም ፡ ተሰጠው ።

፪ ፤ የግሪክ ፡ አውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ዘመቻ ፡ ብቻ ፡ ለእስክንድር ፡ ስለተገዙ ፡ ወዲያው ፤ የግሪክ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጦ ፡ በፋርሶች ፡ ላይ ፡ ዘመተ ። ፋርሶችን ፡ ለመውጋት ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲወጣ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ሺሕ ፡ ወታደር ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ነው ።

፫ ፤ በሒሌስፖንት ፡ ተሻግሮ ፡ በትንሹ ፡ እስያ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ተጓዘ ። ገና ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ድንበር ፡ ሳይደርስ ፡ ዳርዮስ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ የሰበሰበው ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሲወጣ ፡ ገጠመው ። እስክንድር ፤ ይህን ድል ፡ አድርጎ ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ወታደር ፡ ገደለበት ።

፬ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ዳርዮስ ፡ ከፊተኛው ፡ የበለጠ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆን ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ ሰበሰበና ፡ በሠራዊት ፡ ተከቦ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሠረገላ ፡ ተቀምጦ ፡ አረቢላ ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ወደ ፡ ውጊያው ፡ ስፍራ ፡ ቀረበ ። በዙሪያው ፡ ያሉት የንጉሡን ፡ ሕይወት ፡ ጠባቂ ፡ የተባሉ ፡ ጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

፭ ፤ ጽኑ ፡ ውጊት ፡ ሆነና ፡ ፋርሶችም ፡ ክፉኛ ፡ ተዋጉ ። ዳሩ ፡ ግን ፤ በመጨረሻው ፡ ጦሩ ፡ ሲጠመርርባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ተፈተለኩ ። የሚያሳዝነው ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በፈረስ ፡ ተጋብቶ ከውጊያው ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ለመሸምጠጥ ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ቀረው ፡ ፊት ፡ በፋርስ ፡ ታሪክ ፡ እንደነገርኋችሁ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የገዛ ፡ ዜጎቹ ፡ የሚሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ገደሉት ።

፮ ፤ ከድሉ ፡ በኋላ ፡ እስክንድር ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ፔርሲፖሊስ ፡ ተጓዘ ። ይህም ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ የተከማቸበት ፡ ያጌጠ ፡ ከተማ ፡ ነበር ። በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደባባይ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የዘርስስ ፡ ሐውልት ፡ ቆሞበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የመቄዶንያ ፡ ወታደሮች ፡ ገልብጠው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አንከባለሉት ።

፯ እስክንድር ፡ በፋርስ ፡ ከተማ ፡ በፔርሲፖሊስ ፡ ሳለ ፡ በዝሙትና ፡ በመጠጥ ፡ ተታለለ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የአቴና ፡ ሴት ፡ ከተማውን ፡ ለማቃጠል ፡ አሸናፊውን ፡ አታለለችው ። እንዲሁም ፡ ከተማዪቱ ፡ ከምድር ፡ እስክትጠፋ ፡ ተቃጠለች ።

፰ ፤ ፋርስ ፡ ፈጽሞ ፡ ከተገዛ ፡ በኋላ ፡ እስክንድር ፡ ህንዶችን ፡ ዛሬ ፡ ሂንዱስታን ፡ የሚባሉትን ፡ ወረራቸው ። የዚያ ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ፓሩስ ፡ ይባላል ። ቁመቱ ፡ ወደ ፡ ሰባቱ ፡ ክንድ ፡ ይሆናል ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እስክንድርን ፡ ሊወጋ ፡ መጣ ። ፓሩስ ፡ ሰባት ፡ ተዋጊዎች ፡ ዝሆኖች ፡ ነበሩት ። እስክንድር ፡ ግን ፡ አልነበሩትም ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እስክንድር ፡ ዕድሉ ፡ አጋልጦት ፡ አያውቅምና ፡ ፓሩስ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ተማረከና ፡ ሰንሰለት ፡ በእጁ ፡ አግብቶ ፡ አስቀደመው ።

፲ ፤ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ውርደት ፡ የህንዶች ፡ ንጉሥ ፡ ወደድል ፡ አድራጊው ፡ ድንኳን ፡ ገባ ። የህንዱን ፡ ንጉሥ ፡ ቁመት ፡ አረዛዘሙን ፡ አይቶ ፡ እስክንድር ፡ እጅግ ፡ ተደነቀ ። እርሱ ፡ እንኳ ፡ ታላቅ ፡ አሸናፊ ፡ ሲባል ፡ መጠነኛ ፡ ነበር ። እስክንድር ፡ ምርኮኛውን ፡ «እንደምን ፡ አድርጌ ፡ ላኑርህ ፡» ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፤ ምርኮኛው ፡ ፓሩስ ፡ «እንደ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገህ ፡ አኑረኝ ፡» ብሎ ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ መልስ ፡ እስክንድር ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ተመልሶ ፡ አሰበና ፡ «እኔው ፡ ራሴ ፡ በሱ ፡ ስፍራ ፡ ብሆን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያኖረኝ ፡ እወድ ፡ ኑርዋል ?» ብሎ ፡ ለፓሩስ ፡ የቸርነት ፡ ሥራ ፡ እንዲደረግለት ፡ አሰበ ።

<u>ጥያቄ ።</u>

፩ ፤ አዲሱ ፡ የመቄዶንያ ፡ ንጉሥ ፡ ማነው ፡ ? ለጀግንነቱ ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ አሳየ ።

፪ ፤ የግሪክ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ዋና ፡ ጠቅላይ ፡ የተባለው ፡ ምን ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ከሳየ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ?

በፋርስ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ፡ ? ፋርስ ፡ ከመቄዶንያ ፡ ወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ለመድረስ ፡ ወታደሮቹ ፡ የሄዱት ፡ በየት ፡ ባሕርና ፡ በየት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?

እስክንድርን ፡ የተቃወመው ፡ ማነው ፡ ? ከዳርዮስ ፡ ወገን ፡ ስንት ፡ ሰው ፡ ሞተ ፡ ?

፬ ፤ የዳርዮስን ፡ ጕዞና ፡ የሚሊዮን ፡ እኩሌታ ፡ ስለሚሆነው ፡ ጭፍራው ፡ ተርክ ።

፭ ፤ ዳርዮስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ እስክንድር ፡ ድል ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ወዴት ፡ ሄደ ፡ ? ፔርሴፖሊስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከአቴን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? የዘርስስ ፡ ሐውልት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፤ በፔርሲፖሊስ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? አለክሳንድር ፡ ቀጥሎ ፡ የትኛውን ፡ አገር ፡ ወረረ ፡ ?

፰ ፤ ፓሩስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ፓሩስ ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ እንስሶች ፡ ነበሩት ፡ ?

ማን ፡ አሸነፈ ፡ ? ፓሩስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ስለ ፡ እስክንድርና ፡ ስለ ፡ ፓሩስ ፡ ግጭት ፡ ተናገር ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፹፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ እስክንድር ፡ ሥራ ፡ መክናወን ።

፩ ፤ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እስክንድር ፡ በሥራው ፡ እጅግ ፡ የተመሰገነና ፡ የከበረ ፡ አካሄድ ፡ አሳይቶአል ። ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ እስኪበላሸበት ፡ ድረስ ፡ ማንኛውም ፡ የሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይከናወንለት ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ ራሱን ፡ ከአማልክት ፡ ጋር ፡ ለማስተካከል ፡ ተመኘ ።

፪ ፤ እስክንድር ፡ አምላክነት ፡ መመኘቱ ፡ ይቈይና ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ለሰው ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ። ከሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የሚከፋው ፡ ከንጉሥ ፡ ፊሊጶ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋ ፡ የነበረውን ፡ ክሊቱስ ፡ የተባለውን ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ መግደሉ ፡ ነው ። ይኸው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከጦርነት ፡ ውስጥ ፡ የእስክንድርን ፡ ሕይወት ፡ ያዳነ ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንደልቡ ፡ እንዲናገር ፡ ተፈቅዶለት ፡ ነበር ።

፫ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ እስክንድር ፡ ያለመጠን ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ ከሰከረ ፡ በኋላ ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ጉራ ፡ እየተናገረ ፡ ይፎልል ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ ከሽማግሌው ፡ ከክሊቱስ ፡ ይልቅ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባቸው ፡ ሌሎች እንዳሉ ፡ አብልጦ ፡ ተናገረ ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ አባቱ ፡ ፊሊጶ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ እንዳደረገ ፡ ተናገረ ።

፬ ፤ ንጉሡ ፡ ወዲያው ፡ ተቈጣና ፡ በዙሪያው ፡ ከቆሙት ፡ አሽከሮች ፡ ከንዱ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ነጥቆ ፡ እንደማይድን ፡ አድርጎ ፡ ክሊቱስን ፡ ወጋው ፤ በደም ፡ የተ

በከለ ፡ የሽማግሌው ፡ ሬሳ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ተዘርሮ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሀት ፡ ያዘው ። ደግሞ ፡ የንጉሡን ፡ ሕይወት ፡ ጠባቂ ፡ የተባለውን ፡ የገዛ ፡ ዘበኛውን ፡ አረደው ።

፳፬ ፤ እስክንድርን ፡ ሕሊናው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልወቀሰውም ። አሁንም ፡ አምላክነትና ፡ የጁፒተር ፡ አሞን ፡ ልጅ ፡ መሆን ፡ ከአሳቡ ፡ አልጠፋም ። ከሌስቲኒስ ፡ የተባለ ፡ ፈላስፋ ፡ አልሰግድልህም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ ስላለው ፡ ከፈላስፋው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ቅያሜ ፡ ነበረው ፤ ምንም ፡ ሌላ ፡ አበሳ ፡ ሳይኖርበት ፡ ከሌስቲኒስን ፡ በብረት ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ አግብቶ ፡ ተስፋ ፡ እስኪቈርጥ ፡ መከራ ፡ አስቀበለው ።

፳፭ ፤ እስክንድር ፡ ከህንድ ፡ ወደፋርስ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አገኘው ። ይኸውም ፤ የዋናው ፡ ወዳጁ ፡ የሔፌሽን ፡ ሞት ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ እስክንድር ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ምግብ ፡ ሳይቀምስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ።

፳፮ ፤ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ቆለለ ። ቢገመት ፡ ላንድ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ በሆነ ፡ ነበር ።

፳፯ ፤ ለመቃብሩ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሽቱና ፤ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የከበረ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበና ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ የሔፌሽንን ፡ ሬሳ ፡ አጋድሞ ፡ እስክንድር ፡ ከታች ፡ እሳት ፡ ለቀቀበት ፤ የወዳጁ ፡ ሬሳ ፡ አመድ ፡ እየሆነ ፡ ሲያልቅ ፡ ቆሞ ፡ እየተመለከተ ፡ ያዝን ፡ ነበር ።

፳፰ ፤ በሔፌሽን ፡ የደረሰበትን ፡ መከራ ፡ ተመልክቶ ፡ ቢጠነቀቅ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ታላቁ ፡ እስክንድር ፡ በወይን ፡ የሚጠፋበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ። በባቢሎን ፡ በተደረገው ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ወይን ፡ ሲጠጣ ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ታመመና ፡ አሸናፊ ፡ የነበረው ፡ ወዲያው ፡ በሞት ፡ ተሸነፈ ።

፳፱ ፤ የእስክንድርን ፡ ሥራ ፡ ለመገመት ፤ የመቄዶንያ ፡ ወታደሮች ፡ አንድ ፡ ወንበዴ ፡ ቀማኛ ፡ አስረው ፡ ነበር ። ማን ፡ አዘዘህና ፡ ነው ፡ ? ሰውንስ ፡ የምትቀማ ፡ በማን ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ? ብሎ ፡ ወንበዴውን ፡ እስክንድር ፡ ቢጠይቀው ፡ «ወንበዴነቴ ፡ አንተ ፡ አሸናፊ ፡ በሆንኸበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንተና ፡ በኔ ፡ መኻከል ፡ ልዩነቱ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ አሉኝ ፡ የሚጠፉው ፡ ጥቂት ፡ ነው ። አንተም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ አለህ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ የምታጠፋው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ » ብሎ ፡ ወንበዴው ፡ መለሰ ።

፴ ፤ ባሸናፊውና ፡ በወንበዴው ፡ መኻከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ሁልግዜ ፡ መገለጥ ፡ ይገባዋል ። እስክንድር ፡ ለዓለም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፤ ጠቃሚ ፡ የነበረ ፡ ይመስል ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ሬሳውን ፡ ግብፅ ፡ እስክንድርያ ፡ በከበረ ፡ ሣጥን ፡ አኑረው ፡ ግብፆችም ፡ ለአምላክ ፡ የሚገባውን ፡ ክብረት ፡ አደረጉለት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ እስክንድር ፡ ምን ፡ አደረገ ፡? አካሄዱን ፡ ያበላሸበት ፡ ምንድነው ፡? ራሱን ፡ ማን ለማድረግ ፡ አሰበ ፡?
፪ ፡ የእስክንድር ፡ ሥራው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡? ክሊቱስ ፡ ማነው ፡?
፫—፬ ፡ ስለ ፡ ክሊቱስ ፡ መገደል ፡ ተናገር ።
፭ ፡ እስክንድር ፡ ማን ፡ እንዳይበል ፡ ከለከለ ፡? ማነው ፡ ካሊስቴስ ፡?
፮ ፡ ሔፊስሽን ፡ ማነው ፡? የሞተበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ፡?
፯ ፡ ሬሳውን ፡ እስክንድር ፡ ምን ፡ አደረገው ፡?
፰ ፡ እስክንድር ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሞተ ፡? የሞተው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡? ባቢሎን ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ? ስለ ፡ ባሕር ፡ ወንበዴ ፡ ተናገር ። እስክንድር ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ተደረገለት ፡?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ጎል ፡ የተባሉ ፡ የፈረንሳይ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ገቡ ።

፩ ፡ እስክንድር ፡ በሚሞትበት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ሊሞት ፡ ሲያጣጥር ፡ የገዛ ፡ አሽከሮቹ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት ። ከግሪክ ፡ አገር ፡ ጀምረህ ፡ እስከ ፡ ህንድ ፡ ድረስ ፡ ሌሎችንም ፡ አገሮች ፡ ጨምረህ ፡ ያቀናኻቸውን ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለማ ነው ፡ የምትሰጠው ፡? ቢሉት ፡ በጣም ፡ ችሎት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ነዋ ! ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

፪ ፡ ይህም ፡ መልስ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ከተዋቸው ፡ ሰዎች ፡ መኻከል ፡ የርሱን ፡ ቀንበር ፡ ለመሸከም ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ፡ ማለትን ፡ ይገልጻል ። የሚገባው ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ እንኳ ፡ ያ ፡ የማይገባው ፡ ሌላው ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጠው ፡ አይፈቅድም ። ስለዚህ ፡ የእስክንድር ፡ መንግሥት ፡ ለሠላሳ ፡ ሦስት ፡ መኳንንት ፡ ተከፈለ ።

፫ ፡ ከነዚህም ፡ አለቆች ፡ በጣም ፡ ኀይል ፡ የተሰማቸው ፡ ከድርሻቸው ፡ በላይ ፡ አብልጠው ፡ ለመያዝ ፡ ፈለጉ ። ፫፻፩ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ከነዚሁ ፡ አለቆች ፡ አራቱ ፡ ብቻ ፡ ሁሉንም ፡ ጠቅለው ፡ ያዙ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስክንድር ፡ ከሞተ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሆኖት ፡ ነበር ። ልጆቹንና ፡ ተወላጆቹንም ፡ ሁሉ ፡ የራሳቸውን ፡ ክብር ፡ ብቻ ፡ የሚፈልጉ ፡ የገዛ ፡ መኳንንቱ ፡ ፈጅዋቸው ።

፬ ፡ ግሪኮች ፡ ግን ፡ የእስክንድርን ፡ ሞት ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ነጻነታቸውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመመለስ ፡ ይፈትኑ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መታገላቸው ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ። አገሩ ፡ ካሳንድር ፡ በተባለ ፡ ሰው ፡ ሲገዛ ፡ ቈይቶ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ካሳንድር ፡ ደጃዝማች ፡ ተብሎ ፡ የእስክንድር ፡ የፈረሰኞች ፡ ያንጋቾች ፡ አላቃ ፡ የነበረ ፡ ነው ። ደጃዝማች ፡ ካሳንድርም ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ሞተ ። ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡

ወደፊት ፣ የግሪክ ፣ ታሪክ ፣ በደልንና ፣ ሽፍትንትን ፤ አለመታደልንም ፣ ይተ ርከልናል ፣ እንጂ ፣ ሌላ ፣ ምንም ፣ የሆነ ፣ ነገር ፣ የለውም ።

፳፭ ፤ ፬፻—፫ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ ጎልስ ፣ ወይም ፣ ኬልትስ ፣ የተባሉ ፣ ሕዝብ ፣ ግሪክን ፣ ወረሩት ፣ እነዚህም ፣ ዛሬ ፣ ፈረንሳይ ፣ በሚባለው ፣ አገር ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ። አራዊት ፣ ሕዝብ ፣ ነበሩ ። አለቃቸውም ፣ ቤርኑስ ፣ የተባለ ፣ ነበር ። ብዛታቸው ፣ አንድ ፣ መቶ ፣ ስድሳ ፣ አምስት ፣ ሺሕ ፣ ይሆናሉ ።

፳፮ ፤ ቤርኑስ ፣ በምንም ፣ አልታገደ ። ስመ ፣ ጥሩ ፣ በሆነው ፣ በአፖሎ ፣ ቤተ ፣ ጣዖት ፣ ብዙ ፣ መዝገብ ፣ እንደ ፣ ተሰበሰበ ፣ ስለ ፣ ሰማ ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ የተከማቸ ፣ መዝገብ ፣ እንደኔ ፣ ላለ ፣ ለትልቅ ፣ ሰው ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ ለአፖሎ ፣ ምንም ፣ አይረባውም ፣ ብሎ ፣ ያንን ፣ ገብቶ ፣ ለመዝረፍ ፣ ወደዴልፊ ፣ ተጓዘ ።

፳፯ ፤ ቤርኑስ ፣ እንዲሁ ፣ እነዚያን ፣ አራዊት ፣ ወታደሮቹን ፣ ወደ ፣ ቤተ ፣ ጣዖቱ ፣ እየመ ራቸው ፣ በተቃረቡ ፣ ጊዜ ፣ በዕብነ ፣ በረድ ፣ ተሠርቶ ፣ ጎልቶ ፣ የሚታየው ፣ የሕ ንጻው ፣ ግንባር ፣ ገና ፣ ብቅ ፣ ሲሉ ፣ ታያቸው ። ይህም ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ አንድ ፣ ቅዱስ ፣ ስፍራ ፣ ተብሎ ፣ የሚታሰብ ፣ ነበር ። ምስጢር ፣ ያለው ፣ ጥበብ ፣ ብዙ ፣ ትንቢትና ፣ ተአምራት ፣ የሚመጣው ፣ ከዚሁ ፣ ነበር ።

፳፰ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ከጎሎች ፣ ጦር ፣ ጭፍራ ፣ መኻከል ፣ አንዱ ፣ አውሬ ፣ ወታደር ፣ በጮኸ ፣ ጊዜ ፣ ቤተ ፣ ጣዖቱን ፣ ለመዝረፍ ፣ ወደ ፣ መቅደሱ ፣ ሊሮጡ ፣ ሲከጅሉ ፣ ያን ፣ ጊዜውን ፣ ጽኑ ፣ ነፋስ ፣ ተነሣና ፣ መብረቅና ፣ ነጐድጓድም ፣ ሆነ ። ወዲያው ፣ በቅጽበት ፣ የሚያስፈራ ፣ የምድር ፣ መናወጥ ፣ ሆነና ፣ ከታች ፣ መሬቱን ፣ ሲያናው ጸው ፣ ጊዜ ፣ ይህ ፣ ሁኔታ ፣ የጎል ፣ ወታደሮችን ፣ አስፈራ ።

፳፱ ፤ የግሪክም ፣ ጭፍሮች ፣ ቤተ ፣ መቅደሳቸውን ፣ ለማዳንና ፣ ለመከላከል ፣ ሊዋጉ ፣ ተሰናዱ ። አራዊት ፣ በሆኑ ፣ በጎል ፣ ጭፍሮች ፣ ሁከት ፣ እንደ ፣ ተነሣባቸው ፣ በዩ ፣ ጊዜ ፣ ግሪኮች ፣ በሰይፍ ፣ ገቡባቸው ። ጊዜው ፣ ጨልሞ ፣ ነበርና ፣ ጎሎች ፣ ወገኖቻቸውንና ፣ ጠላቶቻቸውን ፣ ሊለዩ ፣ ስለ ፣ አልቻሉ ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ መጋደል ፣ ሆነና ፣ ጦራቸው ፣ ሁሉ ፣ ተበላሸ ።

፴ ፤ የጥንት ፣ ባለታሪኮች ፣ ስለ ፣ ጦርነቱ ፣ የሚናገሩት ፣ እንደዚህ ፣ የመሰለ ፣ ነው ። አብ ልጦ ፣ ብዙ ፣ እንደ ፣ ተወራ ፣ ጥርጥር ፣ የለውም ። ከተወራው ፣ አብዛኙ ፣ የታመነ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ማንም ፣ ሆነ ፣ የጥንት ፣ ግሪኮች ፣ የዚያን ፣ ጊዜ ፣ በጠላቶቻቸው ፣ ላይ ፣ ያገኙት ፣ የመጨረሻው ፣ ድል ፣ ይህ ፣ ነበር ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ በሚሞትበት ፣ አልጋ ፣ ላይ ፣ ተጋድሞ ፣ ሳለ ፣ እስክንድርን ፣ ምን ፣ ብለው ፣ ጠየቁት ፣ ? እርሱ ፣ ምን ፣ ብሎ ፣ መለሰላቸው ፣ ?

፪ ፤ መንግሥቱ ፣ እንዴት ፣ ተከፋፈለ ፣ ?

፫ ፤ ከክርስቶስ ፣ በፊት ፣ ፫፻፲፪ ፣ ዓመት ፣ ሲሆን ፣ ምን ፣ ሆነ ? የእስክንድር ፣ ልጆ ችና ፣ ዘመዶች ፣ እንደምን ፣ ሆኑ ፣ ?

፬ ፤ ግሪክን ፡ ተገዢ ፡ ያደረገው ፡ ማነው ፡ ? ካሳንድር ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ? እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የግሪክ ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፤ ጎሎች ፡ ግሪክን ፡ የወረሩት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ጀኔራላቸው ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ? የጦር ፡ ጭፍራቸው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ ዴልፊ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከአቴን ፡ ከእስፓርታ ፡ ወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ? በዴልፊ ፡ እንዴት ፤ ያለ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ (መቅደስ ፡ )ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ኖሩዋል ፡ ?

፯ ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖቱ ፡ የነበረውን ፡ ጕዞ ፡ ተናገር ። ጎሎችን ፡ ምን ፡ አስፈራቸው ፤ ?

፰ ፤ ግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ጎሎች ፡ እንደምን ፡ ጠፉ ፤ ?

፱ ፤ የጎሎች ፡ ድል ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ተባለ ፤ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ ኤውሮጳ ፤

### ስለ ፤ ግሪክ ፡ ነጻነት ፤ ፍጻሜ ።

፩ ፤ ቀድሞ ፡ ለይቶዋቸው ፡ የነበረ ፡ ኀይላቸው ፡ እንደ ፡ ጠፋባቸው ፡ እንዲሁ ፡ ግሪኮች ፡ የአርነታቸው ፡ ፍቅር ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፋባቸው ። ይህንን ፤ ለማስረዳት የአጊስን ፡ ታሪክ ፡ እተርክላችኋለሁ ። ይህ ፡ አጊ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሕፃን የእስፓርቶች ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ።

፪ ፤ ንጉሥ ፡ አጊ ፡ ለእስፓርታ ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ ጥንት ሊኩርጉዝ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረውን ፡ ደንብና ፡ ሥራት ፡ ለማደስ ፡ ታላቅ ናፍቆት ፡ ነበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ እስፓርቶች ፡ ክፎችና ፡ ልብ ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ሊኩርጉዝ ፡ የሚሉትን ፡ ስም ፡ ፈጽመው ፡ ስለ ፡ ጠሉት ፡ በጠነከረ ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ አሰቡ ።

፫ ፤ ስለዚህ ፡ ሕፃኑን ፡ ንጉሥ ፡ ያዙና ፡ እየጐተቱ ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ። ወዲያው ፡ እንዲሞት ፡ ብለው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረዱበት ፡ ሊገድሉት ፡ ሲወስዱት ፡ ቢያለቅሱለት ፡ «ለኔ ፡ አታልቅሱ ፡ ከገዳዮቼ ፡ ይልቅ ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡ » አላቸው ።

፬ ፤ ወዲያው ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ አጊን ፡ ገደሉት ፤ እናቱና ፡ ሴት ፡ አያቱ ፡ ሞቱን ፡ አልሰሙም ፡ ነበሩና ፡ ሊያዩት ፡ ፈልገው ፡ ወደ ፡ ታሰረበት ፡ ቦታ ፡ ቢመጡ ፡ የአጊ ገዳዮች ፡ ታስሮበት ፡ ወደነ ፡ በረው ፡ ቦታ ፡ እየመሩ ፡ ወሰዱዋቸውና ፡ እያንገላቱ ወደ ፡ ሬሳው ፡ ገፍትረው ፡ ጣሉዋቸው ።

፭ ፤ ከዚህ ፡ ከሚያሰቅቅ ፡ ሁኔታ ፡ በኋላ ፡ እስፓርቶች ፡ ናቢስ ፡ የተባለ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ አንግሠው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ እጅግ ፡ የከፋና ፡ የተረገመ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ለመቅጣት ፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸው ፡ በላያቸው ፡ ያነገሠው ፡ ይመስላል ። ናቢስ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ ነበረችው ። ይኸችም ፡ ሥዕል ፡ ሚስቱን ፡ የምትመስል ፡ እጅግ ፡ ቈንጆ ፡ ሁና ፡ የተሣለች ፡

ነበረች ። ስለ ፡ ልብስዋም ልክ ፡ እቴጌዎች ፡ በሚለብሱት ፡ መጠን ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ልብስ ፡ አልብሱዋታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሥዕሊቱ ፡ ክንድና ፡ ደረት ፡ ብዙ ፡ የሾለ ፡ ብረት ፡ ተተክሎበት ፡ ነበር ።

፯ ፤ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በከበረው ፡ ልብስ ተሸፍኖዋልና ፡ አይታይም ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ናቢስ ፡ ከማንኛውም ፡ ሰው ቢሆን ፡ የግድ ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ጠርቶ ፡ ወደ ፡ ሥዕሊቱ ፡ ዘንድ ፡ ይወስደዋል ። ወዲያው እንግዳው ፡ ሰውዬ ፡ ተመቅረቡ ፡ ሥዕሊቱ ፡ ክንዱዋን ፡ ዘርግታ ፡ በፍጥነት ፡ ሰውዬውን ፡ ወደ ፡ ደረትዋ ፡ አቅፋ ፡ ጠምዛ ፡ ትይዘዋለች ።

፰ ፤ ይህም ፡ በመኪና ፡ የተደረገ ፡ የብልሀት ፡ ሥራ ፡ ነበር ። የሚያሳዝን ፡ ምስኪኑ ፡ ሰውዬ ፡ ለማምለጥ ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡ ይታገል ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጨካኝቱ ፡ ሥዕል ፡ እንደማይላወስ ፡ አድርጋ ፡ አቅፋዋለችና ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ታግሎ ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ። ፃዕረ ፡ ሞት ፡ ሲበዛበት ፡ ናቢስ ፡ የጠየቀውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ካልቀረበ ፡ የሾለው ፡ ወስፌ ፡ ሁሉ ፡ በየሥጋው ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተሰካበት ፡ በዚያው ፡ ይቈያል ።

፱ ፤ በግሪክ ፡ ተወላጆች ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ያህል ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጭክና ፡ ሲደረግ ፡ የግሪኮች ፡ አገር ፡ በሌላ ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ ለመገዛት ፡ ጊዜው ፡ ደረሰ ። ይኸውም ፡ በቶሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመስማት ፡ አንባቢዎች ፡ አያዝኑም ። መቶ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ግሪክ ፡ ለሮም ፡ መንግሥት ፡ ተገዛ ።

፲ ፤ እንደዚህ ፡ አድርጌ ፡ ስለ ጥንት ፡ ግሪክ ፡ አጭር ፡ አሳብ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ። የግሪክ ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ ልብ ፡ የሚነካና ፡ ለትምህርትም ፡ የሚሆን ፡ መልቶበታል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መላውን ፡ ታሪክ ፡ በሌላው ፡ ሰፋ ፡ ባለው ፡ ሥራ ፡ እንድታነቡት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? አጊስ ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ አሰበ ፡ ? እስፓርቶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፪—፫ ፤ ለአጊስ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? አጊስ ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ተናገር ።

፬ ፤ የአጊስ ፡ እናትና ፡ አያቱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፤ ?

፭ ፤ ናቢስ ፡ ማነው ፡ ? ስለ ፡ ምስሉ ፡ ተናገር ።

፮ ፤ ከማንም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ናቢ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፯ ፤ ሮማውያን ፡ ግሪክን ፡ ያሸነፉት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ሮም ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከግሪክ ፤ ከፋርስ ፤ ከህንድ ፤ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፹፱ ፡ አውሮጳ ።

### የግሪክ ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ወደፊት ፡ የግሪክ ፡ ታሪክ ፡ ከሌሎች ፡ ነገድ ፡ ጋር ፡ የተጋጠመና ፡ የተያያዘ ፡ ሆነ ። ግሪኮች ፡ በሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በገዛ ፡ አገራቸው ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ኃይል ፡ አላገኙም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በውስጥዋ ፡ ስለሚገኙት ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቆት ፤ ታሪክ ፡ ተናጋሪዎችና ፡ ደንጊያ ፡ ጠራቢዎች ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ የተከበሩ ፡ ናቸው ።

፪ ፤ በሦስትና ፡ ባራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ የሮማውያን ፡ መንግሥት ፡ ከሁለት ፡ ተከፈለና ፡ የምሥራቅና ፡ የምዕራብ ፡ መንግሥት ፡ ተባለ ። የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ነው ። የጥንት ፡ ግሪክ ፡ ግዛት ፡ ከዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተጨማሪ ፡ ሁኖ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ይባላል ።

፫ ፤ ባ፲፬፻፶፫ ፤ የሮማውያንን ፡ የምሥራቅ ፡ ግዛት ፡ ቱርኮች ፡ ወረሩት ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ግሪክ ፡ ከቱርክ ፡ ሡልጣን ፡ በታች ፡ ወደቀና ፡ ቱርኮች ፡ ፬፻ ፤ ዘመን ፡ ያህል ፡ ግሪኮችን ፡ እንደባርያ ፡ አድርገው ፡ ገዙዋቸው ።

፬ ፤ በኋላ ፡ ባ፲፰፻፳፩ ፡ ለቱርክ ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ ዓመፁና ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ። ውጊያውም ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሆነና ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ በጭከና ፡ ተዋጉ ፤ ግሪኮትንም ፡ ለመርዳት ፡ ብለው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሄዱ ።

፭ ፤ የቀድሞዪቱ ፡ የታወቀችው ፡ ግሪክ ፡ ታሪኩዋን ፡ ከሚያውቁላት ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ተወዳጅታ ፡ ነበር ። ሎርድ ፡ ባየርን ፡ የተባለ ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቂ ፡ የነበረ ፡ ስለ ፡ ስመ ፡ ጥሩዪቱ ፡ ስለ ፡ ግሪክ ፡ ብሎ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ሕይወቱን ፡ አሳለፈ ።

፮ ፤ የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይና ፡ የመስኮብ ፡ መርከቦች ፡ በግሪክ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ተገናኙ ። ሁሉም ፡ ሰር ፡ ኤድዋርድ ፡ ኮድሪንግተን ፡ በተባለ ፡ በእንግሊዝ ፡ አድሚራል ፡ (የመርከቦች ፡ ሹም) ፡ ይታዘዙ ፡ ነበር ። በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፰፻፳፯ ፡ ዓመት ፡ ናቫሪኖ ፡ በተባለች ፡ ጠረፍ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ የነበሩትን የቱርክን ፡ መርከቦች ፡ ገጠሙዋቸው ።

፯ ፤ ቱርኮች ፡ ፈጽመው ፡ ድል ፡ ሆኑና ፡ መርከቦቻቸውም ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሰጠሙ ። አኩሌቶችም ፡ ተቃጠሉ ። ግሪኮችም ፡ ተግፈኛው ፡ ነጻ ፡ ወጡ ።

፰ ፤ ግሪኮች ፡ ለራሳቸው ፡ የሚስማማቸውን ፡ ንጉሥ ፡ ለመምረጥ ፡ ምንም ፡ ስላላሰቡ ፡ እንግሊዝ ፤ ፈረንሳይና ፡ መስኮብ ፡ በንድነት ፡ ሁነው ፡ ንጉሥ ፡ መረጡላቸው ። አዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ያ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የባቫሪያን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ኦቶ ፡ የተባለው ፡ ነው ። ባ፲፰፻፴፪ ፡ ዓመት ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ኦቶ ፡ ዜጎቹን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ለመግዛት ፡ ስለ ፡ አልቻለ ፡ ባ፲፰፻፷፪ ፡ ተሻረና ፡ ግሪክ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በምስለኔ ፡ ተገዛ ።

፱ ፤ ባ፲፰፻፷፪ ፡ ዓመት ፡ ግሪኮች ፡ ንጉሥ ፡ ለመምረጥ ፡ ተሰበሰቡ ። የእንግሊዝን ፡ ንግሥት ፡ የኤልሳቤጥን ፡ ሁለተኛውን ፡ ልጅ ፡ ፕሪንስ ፡ አልፍሬድን ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ሠራዊት ፡ መረጠው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አመራረጥ ፡ እንግሊዝ ፡ አልፈቀደም ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ሁለተኛው ፡ ልጅ ፡ ለንጉሥነት ፡ ተመረጠ ። በኅዳር ፡ ባ፲፰፻፷፫ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ ሄደና ፡ ጂዮርጅ ፡ አንደኛ ፡ ተብሎ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀመጠ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእንግሊዝ ፡ እጅ ፡ ተጠብቀው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ አዮኒያን ፡ የተባሉትን ፡ ደሴቶች ፡ እንግሊዝ ፡ ለግሪክ ፡ ተወለት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? የተከበሩት ፡ በምንድነው ፡ ?

፪ ፤ የሮም ፡ መንግሥት ፡ የተከፈለው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ሁለቱ ፡ ክፍል ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ? ቍስጥንጥንያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
ከአቴን ፤ ከኙዮርክ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ ማን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፡ ?

፫ ፤ ባ፲፬፻፶፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
ግሪክ ፡ በማን ፡ እጅ ፡ ወደቀ ፡ ?
እንደምን ፡ ሆነው ፡ ኖሩ ፡ ?

፬ ፤ ባ፲፰፻፳፩ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

፭ ፤ ግሪኮችን ፡ የረዳቸው ፡ ማነው ፡ ? ግሪኮች ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ አገኙ ፡ ?
ባይሮን ፡ ማነው ፡ ?

፮ ፤ ባንድነት ፡ የነበሩትን ፡ የእንግላንድን ፡ መርከቦች ፡ ያዛቸው ፡ የነበረ ፡ ማነው ፡ ?
ፈረንሳይና ፡ ረሺያ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፯ ፤ ቱርክን ፡ የመቱት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ቱርክ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ግሪክን ፡ ለመልቀቅ ፡ ግዴታ ፡ ሆነባቸውን ፡ ?

፰ ፤ ለግሪኮች ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ማን ፡ ተመረጠ ፡ ? ማን ፡ ይባላል ፡ ?
አገሩ ፡ ወዴት ፡ ነበር ፡ ?
ወደ ፡ ዙፋኑ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወጣ ፡ ? ስለምን ፡ ተሻረ ፡ ?

፱ ፤ ግሪክ ፡ እንደምን ፡ ይገዛል ፡ ?
መጀመሪያ ፡ ለንጉሥነት ፡ ማን ፡ ተመረጠ ፡ ?
ዘውዱን ፡ አለመቀበሉ ፡ ስለምንድነው ፡ ?
በኋላ ፡ ምርጫው ፡ ከማን ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡ ?
የተመረጠው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?